# ንፋሱ ያዘመማቸዉ የእዉቀት ማማዎች

ርእሱ የተቀመጠበት ጥቁርና ነጭ ሰሌዳ የሚያሳየዉ የአዋቂች(የእዉቀት ማማዎች) ላይ የሚደረግ ጫና ከነሱ የሚገኘዉን እዉነተኛ እዉቀት በጥልመት (በዉጫዊ ገጽታዉ ሲታይ) ሊቀይረዉ እንደሚችል ነዉ፡፡ ንፋስ የሚለዉ ቃልም በዘመናት ያየናቸዉን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የነበሩ ጫናዎችን ለማሳዬት ነዉ፡፡ የንፋስ ሀይል ከላይ ወደ ታች የሚወርዱ አስገዳጅ መመሪያዎችን ለመፈጸም የሚደረገዉን እረፍት የለሽ የጥድፊያ ስራዎችን ነዉ፡፡ ንፋሱ የሚያስከትለዉን የሂወትና የንብረት ኪሳራን(መዝመምንና መሰበርን) አንባቢዉ ልብ ይላል፡፡

ህይወት መወለድን፣ ማደግን፣ መድከምን(ብሎም መዝመምና መሰበርን) ሊወክል ይችላል፡፡ የታዋቂዉ ዘፋኝ ለታዋቂ ሟች የተዘፈነ የዘፈን ሀረግ ማንሳት ወደድኩ (*the candle in the wind...*) ለኔ የሚሰጠኝ ትርጉም የንፋሱን የሰዎችን ተስፋ ነጣቂነት ነዉ፡፡ የማን ተስፋ በአንድ በኩል በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ሙሁራንን በሌላ በኩል ንፋሱ ክፉኛ የሚያዉካቸዉን ተማሪዎች ነዉ፡፡

ንብረት ቋሚና አላቂ እቃዎችን ፣ መጽሀፍትን ፣ ቢሮዎችን ፣ ቤተ-መጽሀፍትን ፣ ቤተ-ሙከራዎችን(ዎርክ-ሾፖችን ወዘተ) የሚወክል ነዉ፡፡ ንፋሱ ዉስጣዊና ዉጫዊ መንስኤ ይኖረዋል፡፡ ዝመቱ(ንቅዘቱ) ከዬት መጣ የሚለዉ ሲነፍስ ከማየት ዉጭ ብዙ ግዜ መነሻና መድረሻዉን ለማወቅ ያስቸግራል ከፍጥነቱና ከብርቱነቱ አንጻር ማለት ነዉ፡፡ ሙከራዎች ቢኖሩም ማለቴ ነዉ፡፡

በመሆኑም ጸሀፊዉ በአንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምኅር ስለሆነ ግዜዉን ከመምህራን ባልደረቦቹና ከተማሪዎች ጋር የተቆራኘ ነዉ፡፡ የሚቀርቡ ጭብጦችም የነዚህ መምህራንና ተማሪዎች እዉነተኛ ታሪኮችና የሚታወቁ እዉነታዎች ናቸዉ፡፡  የጋራ ተስፋችንም በሽፋኑ የምትታዬዉን ተሽከርካሪ ማርስ ሮቨርን(Mars Rover) በኛዉ ተቋም ተሰርታ ማዬት መቻል ከብዙዎቹ አንዱ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡

በቅርቡ ስለሆነ ጉዳይ የሚቀጥለዉ ዝርዝር ሀሳብ ያጠነጥናል፡፡ በሀገራችን የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ከእቅዳቸዉ 80% ለሚሆኑ ተመራቂዎች ስራ ማስገኘት መቻል እንዳለባቸዉ ታዘዉ ማቀድ ጀምረዉ ነበር፡፡ ጎሽ! አበጃችሁ አትሉም! ለዚህም የአሉምና (alumna) መከታተያ ቢሮም አቋቁመዉም ነበር፡፡ ለኔ የሚነግረኝ ምናልባትም የሶስት ሚኒስትር መ/ቤቶችን (የስራ ፈጠራ፣ የትምህርት ስልጠና፣ አስቀጣሪ መ/ቤት) ስራ ደርቦ መስራት ነዉ፡፡

ለምንድን ነዉ አሳዉን ከመስጠት ይልቅ ስለ አሳ ማጥመድ ማስተማር ላይ የማናተኩረዉ? ለተማረና ለተመራመረ ይቅርና ፊደል ላልቆጠሩ ወገኖችም የሚሰራ መመሪያ ነዉ፡፡ ይህንም ገና ትምህርት ላይ ሳሉ የስራ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ ይገባል፡፡ የስራ

ልምምድ እዬተደረገ ከሆነም ዉጤቱ መመዘን ያለበት ለተማረና ለተመራመረ የሚመጥን ስራ ይሰራሉ ወይ ነዉ? ይህ ከሆነ በሩቅ አሳቢዎቹ የቢዝነስ ሰዎች ለእንደዚህ ያለ ስራ ኢንቨስት ማድረጋቸዉ አይቀርም፡፡ ከዩኒቨርሲቲዎች የሚጠበቀዉ የኢንቨስተሮችን ቀልብ የሚስብ ለመስራት የተዘጋጁ ተመራቂዎችን ማፍራት ነዉ፡፡

እዚህ ላይ አወንታዊ አመለካከት እያንጸባረቅኩኝ ሊሆን ይችላል አርቀ አሳቢ በማለቴ ነገር ግን ያለእዉቀት የሚመራ ቢዝነስ ዉጤታማ አይሆንም፡፡ ዕዉቀትንና ኢንቨስትመንትን አጣምረዉ የያዙ የቢዝነስ ሰዎችን ለማፍራት ለምን ስራ በዩኒቨርሲቲዎችና(ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት) አጋር ድርጅቶች አይሰሩም፡፡ በአቋራጭ ለማደግ የሚሹ ተመራቂዎችን መንገድ ከወዲሁ ማሳዬት ይገባል፡፡ ገና በይሆናል የዉጭ ሀገር ንሮን እንዲያልሙ ዩኒቨርሲቲዎች (ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት) አስተዋጾ አድርገዋል፡፡

ይህ መራር ሀቅ ነዉ! ዲግሪ ያላቸዉ(እንዲሁም ሌሎች ዜጎች) ለባህርና ለአዉሬ ሲሳይ ሆነዉ ማዬት ለሀገር ጉዳቱ እጥፍ ድርብ ነዉ፡፡ ገፊዉ ንፋስ ሀይል ምንድን ነዉ? ብዙ ገፊ ነገሮች ሊነሱ ይችላሉ ነገር ግን የኔ ትኩረት በተማሩ ስደተኞች ላይ ነዉ፡፡ ስለሆነም ዉጫዊም ዉስጣዊ ገፊዎች አሉ፡፡ *ብሬይን ድሬይን(brain drain)* ዉጫዊዉ ሲሆን ዉስጣዊዉ ደግሞ ከዩኒቨርሲቲዎች(ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት) ጋር የሚያያዝ ነዉ፡፡

በአንድ ተወዳጅ ሚዲያ የተላለፈ ፕሮግራም ማንሳት ፈለግኩኝ በፕሮግራሙ የቀረቡት ሁለት በኢትዮጵያዊ ምግብ ቤት የሚመገቡ በ*ናሳ(NASA)* ዉስጥ የሚሰሩ ተመራማሪዎች ናቸዉ፡፡ የነዚህ ወጣቶች በዚያ ደረጃ መገኘታቸዉ ደስ ይላል፡፡ ሌሎች ሀገሮች ዜጎቻቸዉን በዚህ ደረጃ በመገኘታቸዉ ወደ ሀገራቸዉ ተመልሰዉ ያዩትንና ያካበቱትን እዉቀት ለሀገራቸዉ እድገት አዉለዉታል፡፡ ምን አለፋችሁ እኔም ጭምር ቀደም ሲል የተመኘናትን ማርስ ሮቨርን በተግባር ለሀገራቸዉ አበርክተዋል፡፡ ጥያቄዉ እኛስ የሚለዉ ነዉ? መቼም ማድረግ ለሚፈልግ ከዚህ ግዜ የተሻለ የለም፡፡ ፈተና የበዛበን ግዜ ስለሆነ ለዚህ ደግሞ መዉጫዉ መንገድ እዉቀት ነዉ፡፡ ለምሳሌ ርሀብ፤ በሽታ፤ ጦርነት፤ ድህነት የሀገራችን ፈተናዎች ናቸዉ፡፡

ለምን ዩኒቨርስቲዎቻችን እንደ ማርስ ሮቨር አይነት ከፍ ያለ ነገር አያቅዱም? ቢያንስ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ!! ሰበብ ማባዛት ይቻላል ነገር ግን እንደ ህዳሴ ግድብ ያሉ ከፍ ያሉ እቅዶችን ተግብረናል ሌሎች ፈቀዱም አልፈቀዱም፤፤ ስጋቶች የሉም ማለት አይቻልም፡፡ ዋናዉ ነገር ዋናዎቹን ፈተናዎች ርሀብ፤ በሽታና ድህነትን መዋጋት ነዉ፡፡ ነገር ግን የማይጨበጥ እቅዶችን በማቀድ የማይጨበጥ ዉጤት አዙሪት ትዉልዱን ዋጋ እያስከፈለ ነዉ፡፡ እንደማሳያ የተማረ ስራ አጥ ምንጩ ምንድን ነዉ?

እንደ መምህር የታዘብናቸዉን ልዘርዝር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ቅበላና ምደባ እንዴት ይመስላል? እኔ ዜጎች የትምህርት እድል ማግኘታቸዉ ተገቢ ነዉ እላለሁ ችግሩ የዘመቻ ስራ መሆን የለበትም፡፡ በአንድ ወቅት የጤና ምሩቃንን ቁጥር ለመጨመር በሚል እኔ ያለሁበት ዩኒቨርሲቲ ያለ ዝግጅት ተማሪዎችን መቀበሉን አስታዉሳለሁ፤ በተመሳሳይ አ.አ.ሳ.ቴ(AAASTU) በሚል የሚጠራ ዩኒቨርሲቲ ያለ በቂ ዝግጅት ስራ

መጀመሩን አስታዉሳለሁ፡፡ ሂደቱ በሜጋ ፕሮጀክቶች(የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች) ላይ የታዬዉ አይነት ሀገርን ዋጋ ያስከፈለ ጉዳይ ነዉ፡፡

እነዚህ ጉዳዮች ለምን ሆኑ? ብለን ስንጠይቅ የብልጣብልጦች እጅ እንዳለበት እንረዳለን ምክኒያቱም እቅዶቹ እኔ ምን እጠቀማለሁ በሚል የንፋስ ሀይል ስለሚገፉ ጉዳት አስከትለዋል፡፡ ለምን ካላችሁ የይድረስ ይድረስ ስራ ስለተሰራ ነዉ፡፡ በቂ ዝግጅት ሳይኖር ተማሪዎች ተቀብሎ ማስተማር ዉጤቱ ብስልና ጥሬ አጃምሎ ማዉጣት ነዉ፡፡ ለጤና ባለሞያዎች ሲሆን ደግሞ የሞያ ግድፈት እንዲፈጠርና የህይወት ዋጋ ስለሚያስከፍል አደገኛ ነዉ፡፡ በሁለተኛ የተመላከተዉ ጉዳቱ ደግሞ ተቋሙ ላንድ ማርክ(land mark) ተደርጎ ታስቦ በመከፈቱ ነዉ፡፡ ምክኒያቱም ለዬት ባለ መልኩ ተማሪዎችን በዉድድር መርጦ እንዲቀበል ይደረጋል ነገር ግን ስሙና ወቅታዊ ቁመናዉ አብሮ አይሄድም ነበር፡፡ ስኳር ፕሮጀክቶች በአረም ተዉጠዉ መቅረታቸዉ ገና ከእቅዱ ጀምሮ ብልጣብልጦች ያመቻመቹት ነገር ስለሆነ ነዉ፡፡

ንፋሱ ሌላ ምን አደረገ? ካላችሁ ደግሞ በወቅቱ ተማሪዎችን ያለዝግጅት የተቀበለዉ የዩኒቨርሲቲዉ አመራር አዳዲስ በሚከፈቱ ሌሎች ካምፓሶችና ፕሮግራሞች ተደግሟል ምክኒያቱም በርታ ባይ እንጂ ሃይ ባይ አልነበረም፡፡ በአጭሩ መልቲፕላንግ ኢፌክት(multiplying effect) ነበረዉ፤ እስከዬት ድረስ ለሚለዉ ቤቱ ይቁጠረዉ፡፡ በሂደቱ ከፉኛ የተዋከቡት የፈረደባቸዉ መምህራንና ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ እኔ የሚገርመኝ ብስሉ ከጥሬዉ እንዳይለይ ደግሞ በየአመቱ መጀመሪያ ትም/ክፍሉ ከተቀበላቸዉ ተማሪዎች በዬሴሚስተሩ በጅምላ እንዲያልፉ ያቅዳል ብሎም ያደርጋል፡፡ አትሪሽን ሬት(attrition rate) በፐርሰንት ሲሰላ ከ5% ወደታች ዝቅ እንዲል ይደረጋል፡፡ ዩኒቨርስቲዎች የጥራትን ጉዳይ ዝቅ አድርገዉ ተመልክለዉታል ማለት ይቻላል፡፡ ተገልጋዩና ባለድርሻ አካላት የራሳቸዉ መመዘኛ አላቸዉ ይህም ለህይወት ትርጉም ያለዉ መመዘኛ ነዉ፡፡ ዳሩ ለህይወት ትርጉም ወይም ጥቅም ካልሰጠ ምን ዋጋ አለዉ፡፡ ህይወት ምድራዊም ሰማያዊም ዋጋ አለዉ፡፡ ምን አለ ራዕያቸዉ ህይወትን መታደግ ቢሆንና ስለትልልቆቹ ፈተናዎቻችን እዉቀታችንና ጉልበታችንን ብናዉለዉ፡፡

ንፋሱ በሌላ በኩል በሁለተኛ ስላነሳሁት ጉዳይ ያመጣዉ ጭቅጭቅ በሚዲያዎች ቀርቦ ነበር እነዛ ተስፈኛ ተማሪዎች በበኩላችዉ ያነሱት የነበረዉ ከተመረቁ በኋላ ስራ ትቀጠራላችሁ በተጨማሪም ወደ 60 ፐርሰንቱ ደግሞ እስኮላርሽፕ ታገናላችሁ ተብለናል የሚል ነበር፡፡ ተፈላጊ ሆነን መገኘቱ ነዉ ዋናዉ እነ ቻይና ህንድን መመልከት ይቻላል ለሁላችንም ገበያዉ አለ መወዳደር መቻል ነዉ ዋናዉ ጉዳይ፡፡ ለምሳሌ የአረብ ሀገር ገበያ ለሁላችንም አለ ጥያቄዉ መወዳደር መቻል ነዉ፡፡ ከዚያም አልፎ መሄድ ይቻላል ለልመና ካልሆነ በቀር፡፡ እዚህ ላይ ብልጣብልጦች የዋዛ አደሉም ሲያቅዱ የታያቸዉን እነሱ ብቻ ናቸዉ የሚዉቁት፡፡ የስራ እድሉንም፤ የትምህርት እድሉንም ጠቅልለዉት ሊሆን ይችላል፡፡ በወንጀል ላይ ወንጀል መደረብ የነሱ ድፍረታቸዉ ነዉ፡፡

እኔ የማዉቀዉን ላንሳ አንዱ እንደተመረቀ በግቢዉ ዉስጥ ሳለ ላሳየዉ የማዋከብ ተግባር ሽልማት ተደርጎ የተሰጠዉ፤ ይህን ተግባሩን መምህር ሆኖ እንዲቀጥለዉ ነዉ፡፡ ሌላ መመዘኛ እንደ ሌሎቹ አላሟላም፡፡ ጉደኛ ነበር በፎቶ አልበሙ ከባለስልጣናት ጋር የተነሳቸዉን ፎቶዎች በያጋጣሚዉ ዲስፕለይ(*display*) እያደረገ ሀላፊዎችን ጭምር አዋክቧቸዋል፡፡ ዋናዉ ፈጣጣነቱ ደግሞ መመዘኛ ሳያሟላ እንደተቀጠረ እየታወቀ ሪከርዱን(*the record*) በመለወጥ በዚህ የዉሸት ሪከርድ አንዳንድ ሙከራዎችን ማድረጉ ነዉ(ከዚህ የባሱ በሚዲያ ስለሰማን ላይደንቀን ይችላል)፡፡ ዳሩ ከሸፈበት ሲባል በግሉ ባደረገዉ ሌላ ተመሳሳይ ሙከራ ተሳክቶለት ለትምህርት ወደ ዉጭ ሄዷል፡፡

የሜጋ ፕሮጀክቶች ጉዳይ ዋጋ ያስከፈለን ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል ዞሮ ዞሮ ስለ ለዉጡ ምክኒያት ሆኖ ከሆነ ደግሞ እንኳን ችግሩ ተቀብሮ አልቀረ ያስብላል፡፡ እንደ ሀገር ግን መካስ አለብን እላለሁ፤ በአንድ በኩል የተመዘበረዉ ሀብት በህጋዊ መንገድ መመለስ አለበት፤ ለተፈጸመ ወንጀል የተሳተፉት ሊጠየቁ ይገባል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በምን አይነት የትምህርት ስርአት ቢያልፉ ነዉ እንዲህ አይነት ተግባር ዉስጥ የገቡት የሚለዉ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ ለምን? ብትሉኝ ብልሽቱ እዛ ይጀምራል ብዬ ስለማስብ ነዉ፡፡ መፍትሄዉም የሚገኘዉ እዚህ አካባቢ በሚሰራ ስራ ነዉ፡፡

እልፍ ስንል ደግሞ በድህ ጎናችን ያካበትነዉ ሀብት አጠቃቀም ጤነኛ እንዳልሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ባለሞያዎችና ህጋዊ የክትትል ስልጣን ያላቸዉ አካላት ይገልጻል፡፡ አሁንም ብልጣብልጦች እናሞኛችሁ ይላሉ እንደምክኒያት በተደጋጋሚ የሚያቀርቡት የተማሪዎች ቅበላን ተግባራዊ ስናገርግ የዘመቻ ስራ ስለሚሰራ መመሪያ ስለሚጣስ የሀብት አጠቃቀም ችግር ይፈጠራል ነዉ፡፡ እንደኔ የተማሪ ቅበላም ቢሆን አግበስብሱ አይባልም፤ መጥኑ ነዉ ትክክለኛዉ፡፡

እኔ የሚያሳስበኝ የድሮ አቅማችንን በድርጅትና በአፈጻጸም ደረጃ እያጣን መሆኑ ነዉ፡፡ ይሄ ደግሞ ይጠበቃል በሁሉም ዘርፍ መመጠን ካልቻልን፡፡ ንፋሱ ከላይም ሲወርድ የተመጠነ አይደለም ግዜም የለም፤ አንዳንድ ግዜ ዩኒቨርስቲዎች ትንፋሽም ያጥራቸዋል፡፡ ይሄን የሚመክት ስልጠናና መዋቅር ያስፈልጋል፡፡ ለብቻም መፍጨርጨርም አያዋጣም ትብብርና እርዳታ ለማግኘት ማማተር ያስፈልጋል፡፡

አንዳንድ *አምቢሼስ*(*ambitious*) የሆኑ በንፋስ የሚተላለፉ እቅዶችን ላንሳ አንዱ በየአምስት አመቱ የሚታቀደዉ የስልጠና ፍላጎት ነዉ፡፡ በ3ኛ ና በ2ኛ ዲግሪ ደረጃ የሚታቀደዉ ማለት ነዉ፤ ዳሩ ሲታቀዱ የቅድሚያ ቅድሚያ ተብለዉ ነዉ፡፡ ግራ የሚሆንብኝ(*the irony*) መካከለኛ ገቢ እንዳላቸዉ ሀገሮች ስናቅድ ነዉ፡፡ ይሄን የምለዉ እነዚህ ስልጠናዎች ሀይ-ቴክ(*high-tech*) መሳሪያ ያላቸዉ ላብራቶሪዎች(*laboratories*) መጠየቃቸዉ ነዉ፡፡ ከትምህርት መስጠት ጀምሮ እስከ ምርምር ስራዎች ድረስ ባለዉ ግዜ ያስፈልጋሉ፡፡ ይሄን ሳናሟላ ብናስመርቅ ተገቢነት የለዉም ምን እየሆነ ነዉ ያለዉ? የተመራቂዎቻችን አለም አቀፍ ተቀባይነት እያጣ ነዉ፡፡ ለክልሎች የሰዉ ሀይል ፍላጎት ብቻ ማሰብ የለብንም፡፡ አንድ

ክልል አለ የተባለዉን ላስታዉስ አስተምር እንጂ አባር አላልኩም የሚል ነዉ ይሄ መፈተሽ አለበት የተመራቂዉ ብቃት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ክልሎች ጫና ማድረግስ አለባችዉ፡፡

አንዳንድ ፕሮግራሞችን ዉጭ ልኮ ማስተማር ተመራጭ ነዉ፡፡ አንዳንድ ብልጣብልጦች ይሄን ላይፈልጉ ይችላሉ ምክኒያቱም እዚህ በማስተማር ተጠቃሚ ካደረጋቸዉ ማለት ነዉ፡፡ ሁሉን ነገር ኤስፕሎይት(*exploit*) ማድረግ ተክነዉበታል፡፡ ለምሳሌ በመገባበዝ አንዱ ያንዱን ኮርስ በማስተማር የገንዘብ ማግኛ መንገዶችን  ይፈጠራሉ፡፡ ይቻላል ግን ሞራል በጠበቀ መንገድ ይሁን፡፡ ስራ ፈጠራ ደግሞ ከጥቅም መፈለግ ጋር ሁልግዜ መሆን የለበትም፤ የህሊና ነጻነት ይፈልጋል፡፡ ካልሆነ እስረኛ ያደርጋል፡፡

ምን አለ ጥቅምን ለበጎ ነገር ስንል ይቅርብን ብንል፤ ይሄ ባህል አሁን አሁን ቀርቷል፡፡ ለምሳሌ አንድን ስራ ለተገቢዉ ባለሞያ አሳልፈን ብንሰጥ፤ በተለይ የትምህርት ስራ ሲሆን ለትክክለኛዉ *ስፔሻላይዝድ* (specialized) ላደረገዉ ሰዉ አሳልፈን ብንሰጥ፡፡ ለምሳሌ *ኤክስፐርቲስ*(*expertise*) በሚጠይቁ ምርምር ስራዎች ማንም ዘዉ ብሎ መግባት አይችልም፤ በተመሳሳይ ሀላፊዉ አንድን ኮርስ ለሚቀርበዉ መስጠት የለበትም፡፡ ይሄ መጠቃቀም ስር ከሰደደ ወዳልሆነ አቅጣጫ ሊያመራ ይችላል(ጾታዊ፤ አካባቢያዊ ወዘተ)፡፡ ያየናቸዉ በካድሬዎች የሚሰሩ ስራዎች ስለነበሩ ነዉ ማለትም ሁሉን መጠቅለል አንዱ ነዉ፡፡

ይሄ ጉዳይ ስንቶችን ተስፋ አስቆርጦ አገራቸዉን ጥለዉ እንዲሄዱ አድርጎል ምክኒያቱም አንዱ ሁሉን ከጠቀለለዉ ሌሎች ምን ይሁኑ፡፡ ወይም እነሱም አለን ወደ ሚሉት የራሳቸዉ አካባቢ እንዲፈናቀሉ አድርጎል፡፡ ዩኒቨርስቲዎች አካባቢም ጉልበተኞች ነበሩ ቢያንስ ሌላ ሀይልን በመተማመን፡፡ በዚህም ረገድ አንዳንድ ልዩ የሚያደርጋቸዉን ታዝበናል፡፡ በኢኮኖሚ አቅም አጎልብተዋል፤ አሁን አሁን ማንም አይነካንም ማለታቸዉ አይቀርም ሀላፊነትን በመጣስ ረገድ፡፡ ለምሳሌ አንድ ምስኪን የትም/ክፍል ሀላፊ በነሱ ረገድ ድፍረት ሊያጣ ይችላል፡፡ ለዚህም ነዉ *አካዳሚክ ፕሮሞሽን*(*academic promotion)* ጭምር ሲፈጸም በሚታየዉ ሁኔታ በብርሀን ፍጥነት ሲያሳኩት እናያለን፡፡

ጥራት ሲለካ ለህይወት በሚሰጠዉ ትርጉምና ጥቅም መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም ብስልና ጥሬ መመዘን ያለበት ከዚህ አንጻር ነዉ፡፡ እንደምናዉቀዉ ብስሉም ጥሬዉም ይጠቅማሉ አገልግሎታቸዉ ይለያይ እንጂ የሚጣል ፈጽሞ የለም፡፡ ጥሬዉን በሌላ ዘርፍ በትንሽ ግብአት ዉጤታማ ማድረግ ይቻላል፤ ነገር ግን በንፋስ ሀይል ዩኒቨርስቲዎች ሁሉንም አስመርቀዉ እንዲያወጡ ማድረግ የተማሪዎቹን የሂዎት ጥሪ አለመገንዘብና ብክነትም ነዉ፡፡

ስንቶቹ የዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች በሰለጠኑበት ተሰማርተዉ እዬሰሩ ነዉ? ምን አልባት ስልጠናዉና የእነሱ የሂዎት ጥሪ ባለመጣጣሙ ይሆን? ትዉልዱ ለኢንፎርሜሽን ቅርብ ስለሆነ በዚህ መንገድ የሂወት መንገዱን(ጥሪዉን) ተልሞ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ምርጫዉን ለነሱ ብንተወዉና መንገዳቸዉን የሚያስተካክል ስልጠና ቢሰጣቸዉ፡፡ ለምን? ብትሉኝ የትምህርት አሰጣጡ የተማሪዎችን ሁለንተናዊ የሂዎት አቅጣጫ ለመወሰን ግብአት እንጂ(በአመክንዎ እንዲመሩ) ወሳኝ አይደለም ምክኒያቱም በዉሳኔዉ ሌሎች ተዋናይ

ስላሉ፡፡ በድምሩ ስለትዉልዱ እያወራን ነዉ፤ የትምህርት ስርአቱ ትዉልድ በመቅረጽ ወሳኝ እንዲሆን ለተማሪዎች ሂዎት ትርጉምና ዋጋ ሊኖረዉ ይገባል፤ እንዲያዉም ብስልና ጥሬ ስንል የትምህርት ስርአቱ ዉጤት እንጂ ትዉልዱ(ተማሪዉ) ሊጠየቅ አይገባም፡፡

ለምን? *ስታንዳርዱን*(*the standard*) ያስቀመጠዉ የትምህርት ስርአት አፈጻጸሙን በምን መንገድ ተቆጣጠረዉ የሚለዉ ወሳኝ ነዉ፡፡ በሪሞት ኮንትሮልና(*via remote control*) ለእንጀራዉ ባደረ ካድሬ በሚስጥ የክንዉን ሪፖርት ተነስተን የምናደርገዉ ቁጥጥር ዉጤታማ አይሆንም፡፡ እራሳቸዉን ጭምር እየዋሹ በብልጣብልጥነት እራሳቸዉን በማበልጸግ የተጠመዱ ናቸዉ፡፡ ይቅርታ ይደረግልኝና በ*ሜሪት*(with merit) የሀላፊነት ቦታዎች በባለሞያዎች በዉድድር እዬተያዙ እንደሆነ ልንሰማ እንችላለን፡፡ ዳሩ ምንም የተቀየረ የለም፡፡ አሁንም የኦዲት ሪፖርቶች ብልሽት እንዳለ እያሳዩ ነዉ፡፡ እንዳዉም ስታግኔሽን(*stagnation*) ይታያል ይህም ማለት አዳዲስ ሰዎች አሁንም በነባር ዩኒቨርስቲዎች በሀላፊነት ላይ አይታዩም፡፡ ለምን? ብትሉ የነበረዉ *የኔት ዎርክ*(*net work*) ስራ እንደቀጠለ ነዉ፡፡ የዉድድሩ ሂደትም፤ ዉጤትም ከኔት ዎርክ ስራ የጸዳ አይደለም፤ ብሎም ለቅሬታ እንኳ ዝግ ነዉ፡፡ *ክራይተሪያዉ*(*the criteria*) ለዚህ ያመቻል ብዙ ግዜ ከሚጠበቀዉ የተለዬ ዉጤት ይሆናል፡፡ ቅሬታ እንዳይቀርብ ሂደቱ ድፍን ያለ ነዉ፡፡ ጠቅልለዉ ለሚይዙ አመች ነዉ፤ ለምን? ብትሉኝ ከመስራት ይልቅ ደብዳቤዎችን እያጻፉ የተለየ ጥቅም ፈላጊዎች እዬበዙ ነዉ፡፡

ብልጣብልጦች በኔት-ዎርክ ተሳስረዉ የሚሰሩትን ሰራ ለማስብ የሚከብድ ነዉ፡፡ እንዴት አልመዉ እንደሚንቀሳቀሱ ይገርማል፡፡ ለምሳሌ ለትምህርት ከመሄዳችዉ በፊት የያዙት ስልጣን ተመልሰዉ የማያገኙት ከሆነ ጭራሽ አይሄዱም፤ ጥቅም ይቀርባቸዋል፡፡ ዋስትና ሲያገኙ ብቻ ይሄዳሉ ወይም የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ወደ ህንድ ለትምህርት የሚሄዱ ከሆነ የተለዬ ጥቅም(*privilege*) ለማግኘት ይጥራሉ ከሀገርም ከዉጭ ምንጭ፡፡ በሀገር ዉስጥ ተመልሰዉ ወደ ስልጣን እንዲሚመለሱ ስለሚታወቅ ልወደድ ባይ እነሱን ለማስደሰት ይሰረል፡፡ ለምሳሌ በቁሳቁስ(*ላፕቶፕ ይዘዉ ይሄዳሉ*)፤ ወደ ሀገር ወጭ ተሸፍኖላቸዉ በተደጋጋሚ ይመላለሳሉ፤ ትምህርት ሳይጨርሱ በሀላፊነት ቦታ ይሰራሉ፤ ይጠቀማሉ፡፡ ዉጭ እያሉም በተለዬ ሁኔታ ይጠቀማሉ(የተለየ ድጎማ ያገኛሉ)፡፡ ጨርሰዉ ከተመለሱ በኋላ ተጽእኖቸዉ ይጨምራል፡፡ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተጽእኖ ይኖራቸዋል፤ ኔተ-ዎርኩ ስለሰፋ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በራሳቸዉ ጥረት ባገኙት የትምህርት እድል ወደ ተለያዩ ሀገሮች ሄደዉ ሲመለሱ ልክ በሌሎች ሀገሮች እንዳየነዉ የማርስ ሮቨርን ታሪክ በሀገራቸዉ ለመድገም የምርምር *ግራንት*(*grant*)ና ፕሮጀክቶችን አሸንፈዉ ተስፋ ሰንቀዉ ይመላለሳሉ፡፡ በዚህ መንገድ የላብራቶሪ መሳሪያዎችን ማሟላት ይቻላል ብሎም ደረጃዉን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት ያስችላል፡፡ ሶፍት-ዌሮችንና ማኑዋሎችን(*softwares and manuals*) ይዘዉ ይመለሳሉ፤ ከመጽሀፍትና መሰል ነገሮች በተጨማሪ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ደረጃዉን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ እንዲህ ነዉ ከፍ ያለ ነገር ማድረግ ማለት፡፡ ትዉልዱ በዚህ መንገድ መቅረጽ ከማርስ ሮቨር ፕሮጀክት አያንስም፡፡

ደሮ ብታልም ጥሬዋን ከሆነ ነገሩ የትም አያደርስም ሆድ ከመሙላት ዉጭ፤ የተማረ ሰዉ ህልም ደግሞ ከደሮዋ ካልተሻለ ዉድቀት ነዉ፡፡ ተማሪዎች ከኛ ምን ይማራሉ?፤ ያስተማረችን ሀገርስ ምን ትጠቀማለች? በአቋራጭ የሚደረግ ሩጫ ስንቶችን ከመንገዳቸዉ በአጭር አስቀርቷቸዋል፤ ቤቱ ይቁጠረዉ? የዩኒቨርስቲዎችን ደረጃስ የት አደረሰዉ? ግዙፍ ህንጻ፤ ግዙፍ ግቢ፤ ዉስጣዊ አሰራርን አያሳይም ከመሸፈን ዉጭ፡፡ ዩኒቨርስቲዎች አዲስ አሰራር ባያፈልቁም ቅሉ፤ ከሌሎች ለምን መቅሰም አይሞክሩም፤ ቢሆን ቢሆን የመሪነት ሚና(*leading role*) መጫወት ነበረባቸዉ፡፡ ለራሳቸዉም አልሆኑም፤ ለዚህ ማሳያዉ በየፓርላማዉ ስብሰባ የሚነሱት በሚያሳዩት የአፈጻጸም ጉድለት ነዉ፡፡ ግራ ያጋባል የት ጠብቀናቸዉ የት አገኘናቸዉ? የትስ ይደርሳሉ በዚህ አያያዛቸዉ? የሁሉም ጥያቄ ነዉ፡፡

እስቲ መጋረጃዉን ግልጥልጥ እናድርገዉ፤ ዩኒቨርስቲዎች የሚወዳደሩት በሁሉም ዘርፍ ፕሮግራሞች ለመክፈት ነዉ በተለይ አዳዲሶቹ ዩኒቨርስቲዎች በሌላ ነገር ገና ሆነዉ በፕሮግራሞች ቁጥር በማይታመን ፍጥነት አስፋፍተዋል፤ ይሄ ተላላፊ የሆነ ችግር ነዉ፡፡ ይህ ንፋስ አመጣሽ ችግር ደረጃዉ ይለያይ እንጂ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች(across the board) አለ፡፡ ምክኒያቱም ትምህርትን ማዳረስ(expansion) ጋር ይያያዛል የፖሊሲ ድጋፍ አለዉ በመሆኑም ይሄን ማድረግ ይበረታታል፤ ስለሆነም ለሪፖርትም ያመቻል ያስመሰግናልም፡፡ ጥራትና ቁጥር መስቀለኛ መንገድ ላይ መገናኘታቸዉ አይቀርም የአንድ ጉዳይ ሁለት ገጽታ ሆነዉ፤ ሁለቱን በአንድ ላይ ለማሟላት ዩኒቨርስቲዎች ሲቸገሩ ይታያል፡፡ መስቀለኛ መንገዱን ለማለፍ የትምህርት ጥራት ለግዜዉም ቢሆን ይገፈተራል ሆኖም የተፈጠሮ ህግ ሆነና ሁልግዜ ይሄን ማድረግ አይቻልም፤ በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም ይባል የለም፡፡ ተሳፋሪዎች ምቾት ሲያጡ መልሰዉ የመጡበትን መስቀለኛ መንገድ ይረግማሉ፡፡ የተፈጥሮ ህግም ሆነና ላይመለሱ ነገር፤ ስህተትን በስህተትነቱ መዝግቦ በጉድለት በመያዝ እዳ ያስከፍለናል፤ ከአእምሮ ጸጸት በተጨማሪ፡፡

ስህተቱን ለማረም ደግሞ የሚደረገዉ ፕሮግራሞችን ማጠፍ ነዉ፤ ከለፋንና ዝግጅት ከተደረገ በኋላ መሆኑ ነዉ፡፡ በዉጭም ደረጃ ይጎዳናል በብክነት ምክኒያት(*not cost effective*)፡፡ ሌላ ሌላዉን ቤቱ ይቁጠረዉ፡፡ ስህተት መደጋገምስ ምን አመጣዉ አንዱ ካንዱ አይማርም!! አዳዲሶቹ ፕሮግራሞች ደግሞ ራሳቸዉን ችለዉ ቢቆሙ ጥሩ ነበር፤ ከዚህ በፊት የነበሩ ፕሮግራሞች በሰዉ ሀይል፤ በፋይናንስ፤ በማቴሪያል ስለሚሻሙ የሚጋባ በሽታ አለ፡፡ ሁሉን ሽባ ሊያደርግ ይችላል በተለይ ከጥራት አንጻር፡፡ ራስ ሳይጠና ጉተና ይባል የለ፡፡ እንዴት መንግስትን ጭምር የሚያማክሩ የእዉቀት ማማ ያልናቸዉ የዩኒቨርስቲ ሙሁራን የእለት ተለት ችግሮቻችዉን ከሞያ አንጻር መልክ መልክ ማስያዝ አልቻሉም? የሚያሳትፍ ስላጡ ይሆናል? ከዉነታዉ አልራቀም ምክኒያቱም ጠቅልለዉ የመያዝ አባዜ የተጠናዎታቸዉ እስካሉ ድረስ ማለት ነዉ፡፡ ሌላም የሚሟገቱ(*being not easy going*) ሰዎች ላይፈልጉ ይችላል፤ የተለዩ ጥቅም ላይፈልጉ ይችላሉ፤ ይሄ ደግሞ ልማደኞች ጋር ያጣላቸዋል!! ለምን አይጋፈጡም ልትሉ ይሆናል፤ በጥቅም የታወረ መቼ ይሰማል መልሶ ያደክማል፡፡ ቢያንስ ያዩትን ወይ ጽሁፍ በመጻፍ ግህድ ያወጣሉ፡፡

እነዚህ ጥቅመኞች ፈረስ ያደርሳል እንጂ…የሚባሉ አይነት ናቸዉ! ሚናቸዉ ከዚህ አያልፍም ድርሻቸዉ(*their benefit*) ግን ብዙ ነዉ፡፡ የመኪና አቅርቦት ጀምሮ ያገኛሉ፤ ለቤተሰባቸዉ የሚተርፍ ይሄ ጥቅም እንዳይቀር ማንኛዉንም ዝግጅት አድርገዋል፤ የሚያምኗቸዉን ሰዎች በተለያዩ ቦታ አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ጥቅማቸዉ ሲነካ እንደማስገደጃ ሊጠቀሙባቸዉ ይችላሉ፡፡

ይሄ የጥቅም ትስስር ጉዳቱ ከተቋሙ አልፎ ለሀገር ነዉ፡፡ ይሄ ተላላፊ በሽታ በግዜ ካልታረመ አድማሱን ወደ አካባቢዉ ህብረተሰብ የመዉሰድ እድል አለዉ፡፡ እንዲህ ያለዉ ነገር ከቁጥጥር ዉጭ እዬወጣ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል፡፡